የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

**OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA**

ሰላሳ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፹፪
አዲስ አበባ ሐምሌ ፪ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31th year No 82
Addis Ababa 9st of , Julay2023


## ማውጫ


**ቁጥር ፹፪/፪ሺ፲፭**

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የ፪ሺ፲፭**

**የተጨማሪ በጀት አዋጅ**

**ገፅ..................................................፪ሺ፲፬**


## CONTENTS


**Proclamation No.82 /2023**
**Addis Ababa City Administration 22/23 G.C.**
**Fiscal Year Supplementary Budget proclamation**

**Page -------------------------------------------2014**


## አዋጅ ቁጥር ፹፪/፪ሺ፲፭

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

## የተጨማሪ በጀት አዋጅ

ለ ፳፪ሺ፲፭ የበጀት ዓመት በአዲስ አበባ ከተማ ለሚከናወኑ ሥራዎችና አገልግሎቶች በተጨማሪ የሚያስፈልገውን በጀት አጽድቆ በበጀት ዓመቱ ውስጥ ሥራ ላይ ማዋል አስፈላጊ በመሆኑ፣

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁ.፫፻፷፩/፲፱፺፭ አንቀጽ ፲፬ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተራ ፊደል (ለ) መሠረት ይህን የተጨማሪ በጀት አዋጅ አውጥቷል።

## Proclamation No 82/2023

## SUPPLEMENTARY PROCLAMATION OF ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION

WHERE AS, it has become necessary to approve and disburse Supplementary budget for under taking by the Addis Ababa City Government during the 2022/23 G.C

NOW, THEREFORE, in accordance with letter (B) of Article 14 of the revised charter of the Addis Ababa city government Proclamation no. 361/2003 (as amended), the Addis Ababa city council has issued this Proclamation as follows.

.


**የአንዱ ዋጋ**
**Unit price**

**አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፪ሺ፬፻፵፭**
**Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445**

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ “የ ፪ሺ፲፭ በጀት ዓመት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተጨማሪ በጀት አዋጅ ቁጥር ፹፫/፪ሺ፲፭” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### ፪. የተፈቀደ ተጨማሪ በጀት

ከሐምሌ ፩ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኔ ፴ ቀን ፪ሺ፲፭ በሚፈፀመው በአንድ የበጀት ዓመት ጊዜ ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከሚገኘው ገቢ ላይ ከዚህ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ውስጥ ለተጠቀሱት ሥራዎችና አገልግሎቶች ቀጥሎ እንደተመለከተው፣

**ሀ/ ለማዕከል መ/ቤቶች**

| | |
|---|---|
| ፩.ለመደበኛ ወጪዎች ብር | 985,077,035.56 |
| ፪.ለካፒታል ወጪዎች ብር | 11,268,014,081.06 |
| **የከተማ ድምር** | 12,253,091,116.62 |

**ለ /ለክፍለ ከተሞች**

| | |
|---|---|
| ፩.ለመደበኛ ወጪዎች ብር | 243,480,287.80 |
| ፪.ለካፒታል ወጪዎች ብር | 1,039,994,235.75 |
| **የክፍለ ከተሞች ድምር** | 1,283,474,523.55 |
| **ጠቅላላ ድምር ብር** | 13,536,565,640.17 |

### ፫. ጥቅም ላይ ያልዋ ጥሬ ገንዘብ

፩. ባለፉት ዓመታት ተሰብስቦ ስራ ላይ ያልዋለ ጥሬ ግንዘብ በዚህ አዋጅ እንደ አንድ የገቢ ምንጭ የቀረበው በ፪ሺ፲፭ በተጨማሪ በጀት ስራ ላይ እንዲውል ተፈቅዷል፤

፪. ከላይ የተቀመጠው አጠቃላይ በጀት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጪ ሆኖ እንዲከፈል በዚህ የተጨማሪ በጀት ታዟል።

## PART ONE

## GENERAL

### 1. Short Title

This proclamation may be cited as the “Addis Ababa City Administration 2022/2023 G.C Supplementary Budget Proclamation No 83/2023”

### 2. Allocated Supplementary Budget

The Addis Ababa City Administration Budget is here by appropriated for the fiscal year commencing on July 08/2022 G.C and ending on June 23, 2023 G.C from Addis Ababa City Administration revenues and other funds, for the purposes and services set forth in the schedule here to;

**A/ City Sector Bureaus**

| | |
|---|---|
| 1. For Recurrent Expenditure Birr | 985,077,035.056 |
| 2. .For Capital Expenditure Birr | 11,268,014,081.06 |
| **Total** | **12,253,091,116.62** |

**B/ Sub Cities**

| | |
|---|---|
| 3. Recurrent Expenditure Birr | 243,480,287.80 |
| 4. Capital Expenditure Birr | 1,039,994,235.75 |
| **Sub Cities Total** | **1,283,474,523.55** |
| **Grand Total Birr** | **13,536,565,640.17** |

### 3. Un Used Liquid Cash

1. Revenue Collected in the previous years but not yet Used, is hereby Authorized for 2023 Budget year to put in to use.
2. The City Government of Addis Ababa is hereby authorized to disburse the Supplementary amount mentioned above through this proclamation.

## ክፍል ሁለት

## የበጀት አስተዳደር

### ፬. የከተማ አስተዳደር አካላት ሥልጣን

፩. የክፍለ ከተማ የፋይናንስ ጽህፈት ቤት ኃላፊ ለክፍለ ከተማው ሥራና አገልግሎት በዚህ አዋጅ የተፈቀደለትን በጀት በሚጠይቅበት ጊዜ የፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ ከከተማው አስተዳደር ገቢና ከሌላ ምንጭ እንዲከፍል ተፈቅዶለት ታዟል።

፪. ጉዳዩ የሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ለየመስሪያ ቤቶቻቸው ሥራና አገልግሎት በዚህ አዋጅ የተፈቀደላቸውን በጀት በሚጠይቁበት ጊዜ እንደ አግባብነቱ የፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ ወይም የክፍለ ከተማው ፋይናንስ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ከከተማው አስተዳደር ገቢና ከሌላ ምንጭ ወይም ለክፍለ ከተማው ከተፈቀደው በጀት እንዲከፍል ተፈቅዶለት ታዟል።

፫. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥር የሚተዳደሩት ሆስፒታሎች፣ ጤና ጣቢያዎች፣ ትምህርት ቤቶች፤ የቴክኒክና ሙ.ያ ኮሌጆች፣ የአዲስ አበባ ውኃና ፍሳሽ ባለሥልጣን፣ የቲያትር ቤቶች፣ የትምህርትና ስልጠና ጥራት፤ሙ.ያ ብቃትና ምዘና ባለስልጣን፤ የጉለሌ የዕፅዋት ማዕከል ለበጀት ዓመቱ የተፈቀደላቸውን ጠቅላላ የበጀት መጠን ሳያልፍ ከዘመኑ በጀት ዓመት ገቢያቸው በፋይናንስ ህግ መሰረት ወጪ እያደረጉ ቀጥታ በጥቅም ላይ በማዋል እና ይህንኑ ሂሣብ በመሥሪያ ቤቱ ኘሮግራም፣ የሥራ ክፍል፣ የሂሣብ መደብ መዝግበው በመያዝ በየወሩ ለፋይናንስ ቢሮ ማሳወቅ አለባቸው።

## PART TWO

## BUDGET ADMINSTRATION

### 4. POWER OF THE CITY ADMINISTRATION ORGANS

1. The head of Finance Bureau is here by authorized and directed, up on the Request of the head of the Finance Office of a Sub City to disburse out of the City Administration revenues and other funds the amounts appropriated here in for the purposes and services off a Sub City.

2. The head of Finance Bureau, or head of Finance Office of a Sub City is here by authorized upon the request of the heads of the concerned public bodies, to disburse out of the city Administrations revenues and other funds or out of a Sub City's appropriate budget the amount appropriated here in for the purposes and services of this respective-bodies.

3. Hospitals, Health Centers, Schools, TVET Colleges, Water & Sewerage Authority, Theater houses, Educational and Training Quality, Occupational Competency and Assessment Authority, Gulelle Botanic Garden are allowed to retain and expend within the limit of their budgetary appropriations receipts from the current fiscal year and shall record the amount under its program, department, and codes and shall report monthly to Finance Bureau

፬. የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በዚህ አዋጅ ላይ ላልተመለከቱ ለካፒታልም ሆነ ለመደበኛ ተጨማሪ ሥራዎች ከውጭ ብድር እንዲሁም ከአገር ውስጥም ሆነ ከውጪ ሀገር በዓይነት ወይም በጥሬ ገንዘብ የሚያገኙትን ብድር ወይም እርዳታ በሥራ ላይ በማዋል እና ይህንኑ ሂሣብ በመሥሪያ ቤቱ አርዕስት፣ በንዑስ አርዕስት ኘሮግራም፣ በኘሮጀክት ሥር መዝግበው በተጨማሪ በጀት በመያዝ የበጀት ዓመቱ ከመጠናቀቁ በፊት ለፋይናንስ ቢሮ ሪፖርት ማድረግ አለባቸው፤

፭. <u>የበጀት ዝውውር</u>

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ፶፩/፪ሺ፲ አንቀጽ ፳፪ እና ፳፯ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፡ የበጀት ዝውውር በሚከተለው ሁኔታ ይፈፀማል፤

፩. በመንግሥት መሥያ ቤት ውስጥ የሚደረግ የበጀት ዝውውር

<u>የፋይናንስ ቢሮ ኃላፊዉ</u>:-

ሀ) በመንግሥት መሥያ ቤት ውስጥ መደበኛ በጀትን በሚመለከቱ የወጪ መደቦች ውስጥ የበጀት ዝውውር ለማድረግ፣

ለ) በአንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ በጀትን ከአንድ ካፒታል ፕሮጀክት ወደ ሌላ የካፒታል ፕሮጀክት ለማዛወር፤

ሐ) በበጀት ዓመቱ ላልተያዘለት የካፒታል ፕሮጀክት ቀሪ ግዴታዎች ማስፈፀሚያ የሚውል በጀት ለአስፈጻሚ መሥሪያ ቤቱ ከተፈቀደ የካፒታል በጀት ለማዘዋወር፣

መ) በአንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሥር ያሉ መሥሪያ ቤቶች ሲዋሃዱ ወይም ሲነጣጠሉ በጀቱን ከአንድ ወደሌላው ለማዘዋወር፣ ለከንቲባ አቅርቦ ሲፈቀድለት የመተግበር ሥልጣን ተሰጥቶታል፤

4. Public bodies are hereby authorized to record on their appropriate budgetary head, sub head, project, or program, as the case may be, and undertake all acts necessary for the Utilization of any additional loan or aid in kind and/or cash obtained from foreign or local source for carrying out capital project or recurrent programs, and report to the Finance Bureau before the end of the budget year.

**5. <u>BUDGET TRANSFER</u>**

Without prejudice to the provisions of Article 22 and 27 of the Addis Ababa City Administration Financial Administration proclamation No 51/2017 budget transfer shall be executed as follows:

1. Budget Transfers within Public Bodies

**<u>The Finance Bureau Head may within a Public Body</u>:-**

(a) transfer funds within items of expenditure of the recurrent Budget;

(b) transfer budget from one capital project to another within a Public Body ;

(c) Transfer the budget approved for capital expenditure of the Public Body to finance pending obligations of a project for which no budget is allocated in the current fiscal year;

(e) When programs under one government office are merge or split, to transfer the budget from one to another, the mayor is given the authority to implement it when approved.

፩.፩. የፋይናንስ የቢሮ ኃላፊው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተሰጠውን ሥልጣን በውክልና አግባብ ላለው የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ሊሰጥ ይችላል፣

፪. በከተማው ማዕከል እና በክፍለ ከተማዎች ወይም በመንግሥት መሥሪያ ቤት መካከል የሚደረግ የበጀት ዝውውር፡-

፪.፩ አንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የተፈቀደለትን የመደበኛ በጀት የማይጠ ቀምበት ሆኖ ሲገኝ የፋይናንስ ቢሮ ኃላፊዉ በጀቱን ወደ ሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ለማዘዋወር ይችላል፣

፪.፪ የፋይናንስ ቢሮ ኃላፊው በሚከተሉት ምክንያቶች የአንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የካፒታል በጀት ወደ ሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የካፒታል በጀት እንዲዘዋወር ለከንቲባው በማሳወቅ ሊፈቅድ ይችላል፡-

ሀ) በአንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ ያጋጠመን የካፒታል በጀት እጥረት ለማቃለል በበጀት ዓመቱ ለሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የተፈቀደ እና ጥቅም ላይ ያልዋለን የካፒታል በጀት በማዘዋወር መጠ ቀም አስፈላጊ ሲሆንና ይህም ተጨማሪ በጀት ያስፈለገው ለተፈቀደ የካፒታል ፕሮጀክት መሆኑ ሲረጋገጥ፣

ለ) አስቀድሞ ባሉት ዓመታት ለተፈቀደ እና በበጀት ዓመቱ በጀት ላልተያዘለት ፕሮጀክት ቀሪ ግዴታዎች ማስፈፀሚያ የሚውል በጀት ጥያቄ የቀረበ እንደሆነ፡፡

፫. <u>ከማዕከል ወደ ክፍለ ከተማ የሚደረግ የበጀት ዝውውር</u>

የፋይናንስ ቢሮ ኃላፊው ተራፊ በጀት መኖሩን ሲያረጋግጥ ከማዕከል ወደ ክፍለ ከተማው ወይም ከክፍለ ከተማ ወደ ማዕከል በጀት ሊያዛውር ይችላል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የክፍለ ከተማ ፋይናንስ ጽ/ቤት ኃላፊ የክፍለ ከተማ የሴክተር መ/ቤት ኃላፊዎች በሚያቀርቡት ጥያቄ መሠረት ከክፍለ ከተማ ወደ ማዕከል በጀት ሊያዛውር ይችላል።

1.1 The Finance Bureau Head may delegate the appropriate head of public body to exercise the power vested in him under sub- article 1 of this Article

2. Budget Transfers between Public Bodies & Sub Cities

2.1 The Finance Bureau Head may transfer a recurrent budget from one Public Body to the other if it is ascertained that the Public Body to which the budget is appropriated cannot wholly utilize its budget,

2.2 With the consent of Mayor; The Finance Bureau Head may authorize the transfer of funds from the capital budget of one Public Body to the capital budget of another Public Body under the following conditions

(a) Where a deficiency in one Public Body's capital budget can be met by an offsetting transfer from another Public Body's capital budget approved for that fiscal year provided the capital budget receiving additional funds for approved capital budget.

(b) Where a budget is requested to finance pending obligations of a project approved in previous years for which no budget is allocated in the current fiscal year.

3. <u>Budget Transfers City to Sub cities</u>

The Finance Bureau Head, on the conformation of any unused budget, may transfer a budget from a center Public Body to the sub city or from Sub City to Center public Body. With the same manner the sub city Finance Office Head may transfer budgets from a sub city to a center Public Body.

፬. <u>በጀት ዝውውር መደረጉን ስለማሳወቅ</u>

በዚህ አዋጅ በጀትን የማዛወር ሥልጣን የተሰጣቸው አካላትና ኃላፊዎች የበጀት ዝውውሩን እንደፈቀዱ ወዲያውኑ እንደአግባብነታቸው ለቢሮው ወይም ለጽሕፈት ቤቱ በጽሁፍ ማሳወቅ አለባቸው።

፮. **<u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ ከ ሐምሌ ፪ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፪ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም.**

**አዳነች አቤቤ**
**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

4. <u>Notification of budget transfer</u>

According to this proclamation, the authorized officials and heads of public bodies for transferring budget shall immediately notify in writing to the Finance Bureau or Office as the case may be.

6. **<u>Effective Date</u>**

This Regulation shall enter into force as of this 9 th day of Julay 2023.

**Done at Addis Ababa, this 9th day of July, 2023.**

**Adanech Abiebie**
**Mayor of Addis Ababa City**

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የ፳፻፲፭ በጀት ዓመት የተጨማሪ የገቢና የወጪ አሸፋፈን

### 1. የከተማው ገቢ

| ሀ. የአገር ውስጥ ገቢ | ጠቅላላ ብር |
|---|---|
| የታክስ ገቢዎች | 5,000,000,000.00 |
| ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች | 152,529,568,80 |
| የማዘጋጃ ቤታዊ ገቢዎች | 400,000,000,00 |
| የመንገድ ፈንድ | 232,712,475.07 |
| **የአገር ውስጥ ገቢ ድምር** | **5,785,242,043.87** |
| ከባለፉት ዓመታት ተራፊ ጥሬ ገንዘብ | 4,000,000,000.00 |
| **ለ. እርዳታና ብድር** | |
| የሀገር ውስጥ ብድር | 1,500,000,000.00 |
| የውጭ ዕርዳታ | 242,868,601.30 |
| የውጭ ብድር | 2,008,454,995.00 |
| **የውጭ እርዳታና ብድር ድምር** | **3,751,323,596.30** |
| **የከተማው ጠቅላላ ገቢ ድምር** | **13,536,565,640.17** |

### 2. የከተማው ወጪ

| ሀ. መደበኛ ወጪ | ብር |
|---|---|
| ጠቅላላ የመደበኛ ወጪ | 1,229,420,880.16 |
| ለ. የካፒታል ወጪ | |
| ጠቅላላ የካቢታል ወጪ | 12,307,144,760.01 |
| **ጠቅላላ የወጪ ድምር** | **13,536,565,640.17** |

## ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION 2022/23 REVENUE, EXPENDITURE AND IT'S FINANCING

### 1. REVENUE

| City Administration Revenue Birr | Total Birr |
|---|---|
| A. Domestic Revenue | |
| Tax revenue | 5,000,000,000.00 |
| Non-tax revenue | 152,529,568.80 |
| Municipal service revenue | 400,000,000.00 |
| Road funds | 232,712,475.07 |
| **Total Domestic Revenue** | **5,785,242,043.87** |
| **Liquid Cash From previous years** | **4,000,000,000.00** |
| B. Assistance and Loan | |
| External Assistance | 242,868,601.30 |
| Local Loan | 1,500,000,000.00 |
| External Loan | 2,008,454,995.00 |
| **Assistance and Loan Total** | 3,751,323,596.30 |
| **Total Revenue** | **13,536,565,640.17** |

### 2. EXPENDITURE

| | |
|---|---|
| **A. Recurrent Expenditure** | |
| **Total Recurrent Expenditure** | 1,229,420.880.16 |
| **B. Capital Expenditure** | |
| **Total Capital Expenditure Total** | 12,307,144,760.01 |
| **Total Expenditure** | **13,536,565,640.17** |

## 3. ለ፪ሺ፲፭ በጀት ዓመት ለክፍለ ከተሞች የተጨመረ በጀት

| ክፍለ ከተማ ድምር | መደበኛ ወጪ | ካፒታል ወጪ | ድምር |
|---|---|---|---|
| | **243,480,287.80** | **1,039,994,235.75** | **1,283,474,523.55** |
| **አራዳ ክ/ከተማ** | 7,870,061.00 | 90,000,000.00 | 97,870,061.00 |
| **አዲስ ከተማ ክ/ከተማ** | 12,462,393.00 | 0.00 | 12,462,393.00 |
| **ልደታ ክ/ከተማ** | 14,550,004.80 | 213,326,424.00 | 227,876,428.80 |
| **ቂርቆስ ክ/ከተማ** | | | |
| **የካ ክ/ከተማ** | 12,902,447.00 | 100,000,000.00 | 112,902,447.00 |
| **ቦሌ ክ/ከተማ** | 10,200,000.00 | 86,707,797.75 | 96,907,797.75 |
| **አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ** | 135,200,000.00 | 0.00 | 135,200,000.00 |
| **ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ** | 13,110,887.00 | 0.00 | 13,110,887.00 |
| **ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ** | 13,127,794.00 | 0.00 | 13,127,794.00 |
| **ጉለሌ ክ/ከተማ** | 16,490,221.00 | 330,615,014.00 | 347,105,235.00 |
| **ለሚ ኩራ ክ/ከተማ** | 7,566,480.00 | 219.345,000.00 | 226,911,480.00 |

# 3. Budget for Sub-Cities

| Sub city Total | Recurrent Expenditure | Capital Expenditure | Total |
|---|---|---|---|
| | **243,480,287.80** | **1,039,994,235.75** | **1,283,474,523.55** |
| Arada Sub City | 7,870,061.00 | 90,000,000.00 | 97,870,061.00 |
| Addis Ketema Sub City | 12,462,393.00 | 0.00 | 12,462,393.00 |
| Lideta Sub City | 14,550,004.80 | 213,326,424.00 | 227,876,428.80 |
| Kirkos Sub City | 0.00 | 0.00 | |
| Yeka Sub City | 12,902,447.00 | 100,000,000.00 | 112,902,447.00 |
| Bole Sub City | 10,200,000.00 | 86,707,797.75 | 96,907,797.75 |
| Akaki Kality Sub City | 135,200,000.00 | 0.00 | 135,200,000.00 |
| Nifas Silk Lafto Sub City | 13,110,887.00 | 0.00 | 13,110,887.00 |
| Kolfe Keranio Sub City | 13,127,794.00 | 0.00 | 13,127,794.00 |
| Gulele Sub City | 16,490,221.00 | 330,615,014.00 | 347,105,235.00 |
| Lemmi Kura Sub City | 7,566,480.00 | 219.345,000.00 | 226,911,480.00 |

## ለ2015 በጀት ዓመት የተጨማሪ በጀት ማጠቃለያ

| ተ.ቁ | የመስሪያ ቤት ስም | መደበኛ | ካፒታል | ድምር |
|---|---|---|---|---|
| | ጠቅላላ የተጨማሪ በጀት ድምር | 1,106,790,827.36 | 12,452,931,666.81 | 13,536,565,640.17 |
| 1 | ለትላልቅ ፕሮጀክቶች ግንባታ ጽ/ቤት | - | 3,500,000,000.00 | 3,500,000,000.00 |
| 2 | የአዲስ አበባ ከተማ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን | 400,000,000.00 | 1,963,000,000.00 | 2,363,000,000.00 |
| 3 | የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለስልጣን | - | 2,478,167,470.07 | 2,478,167,470.07 |
| 4 | የአዲስ አበባ ከተማ ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ | | 1,531,628,067.33 | 1,531,628,067.33 |
| 5 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት | 242,000,000.00 | - | 242,000,000.00 |
| 6 | የአዲስ አበባ ከተማ ትራንስፖርት ቢሮ | - | 252,364,162.36 | 252,364,162.36 |
| 7 | የከተማ አውቶቡስ አገልግሎት ድርጅት | - | 300,000,000.00 | 300,000,000.00 |
| 8 | የከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ቢሮ | - | 241,923,916.30 | 241,923,916.30 |
| 9 | አዲስ ሚዲያ ኔት ወርክ | 20,000,000.00 | 20,000,000.00 | 20,000,000.00 |
| 10 | ጀነራል ዊንጌት ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ | - | 5,494,125.00 | 5,494,125.00 |
| 11 | ንፋስ ስልክ ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ | 2,500,000.00 | 5,494,125.00 | 7,994,125.00 |
| 12 | ልደታ ማኑፋክቸሪንግ ኮሌጅ | - | 5,494,125.00 | 5,494,125.00 |
| 13 | ምርታማነት ማሻሻያ ማዕከል | - | 5,494,125.00 | 5,494,125.00 |
| 14 | የአዲስ አበባ ከተማ አመራር አካዳሚ | 3,156,854.00 | 3,156,854.00 | 3,156,854.00 |
| 15 | የአዲስ አበባ ሴቶች ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ | - | 716,234.00 | 716,234.00 |
| 16 | የአ.አ.ከተማ የሲቪል ምዝገባና የነዋሪዎች አገልግሎት ኤጀንሲ | | 67,131.00 | 67,131.00 |
| 17 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ቢሮ | 96,769,533.61 | 14,317.00 | 96,783,850.61 |
| 18 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደደር ም/ቤት ጽ/ቤት | 8,020,800.00 | - | 8,020,800.00 |
| 19 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደደር የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን | 12,192,281.95 | - | 12,192,281.95 |
| 20 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደደር ሰላምና ፀጥታ አስተዳደር ቢሮ | 5,000,000.00 | - | 5,000,000.00 |
| 21 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደደር ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት | 5,447,432.00 | - | 5,447,432.00 |
| 22 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደደር አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን | 1,800,000.00 | - | 1,800,000.00 |
| 23 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ | - | 100,413,000.00 | 100,413,000.00 |
| 24 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ኮርፖሬሽን | - | 701,974,658.00 | 701,974,658.00 |
| 25 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጥሩነሽ ቤጂንግ ሆስፒታል | 31,160,000.00 | 32,000,000.00 | 63,160,000.00 |
| 26 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የካቲት 12 ሆ/ል ሜዲካል ኮሌጅ | 9,691,821.00 | - | 9,691,821.00 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 27 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ራስ ደታ ዳምጠው መታሰቢያ ሆ/ል | 19,671,817.00 | - | 19,671,817.00 |
| 28 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዳግማዊ ምኒሊክ መታሰቢያ ሆ/ል | 5,900,000.00 | - | 5,900,000.00 |
| 29 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት | - | 265,535,121.00 | 265,535,121.00 |
| | **የማዕከል ተቋማት ድምር** | **863,310,539.56** | **11,412,937,431.06** | **12,253,091,116.62** |
| 30 | አራዳ ክፍለ ከተማ | 7,870,061.00 | 90,000,000.00 | 97,870,061.00 |
| 31 | አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ | 12,462,393.00 | - | 12,462,393.00 |
| 32 | ልደታ ክፍለ ከተማ | 14,550,004.80 | 213,326,424.00 | 227,876,428.80 |
| 33 | የካ ክፍለ ከተማ | 12,902,447.00 | 100,000,000.00 | 112,902,447.00 |
| 34 | ቦሌ ክፍለ ከተማ | 10,200,000.00 | 86,707,797.75 | 96,907,797.75 |
| 35 | አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ | 135,200,000.00 | - | 135,200,000.00 |
| 36 | ንፋስ ስልክ ላፍቶ ከተማ | 13,110,887.00 | - | 13,110,887.00 |
| 37 | ኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ | 13,127,794.00 | - | 13,127,794.00 |
| 38 | ጉለሌ ክፍለ ከተማ | 16,490,221.00 | 330,615,014.00 | 347,105,235.00 |
| 39 | ለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ | 7,566,480.00 | 219,345,000.00 | 226,911,480.00 |
| | **የክፍለ ከተሞች ድምር** | **243,480,287.80** | **1,039,994,235.75** | **1,283,474,523.55** |